# ካፒታሊዝም ማለት ምን ማለት ነው ?

ልጅ አባቱን ካፒታሊዝም ማለት ምን ማለት እንደሆን እንዲያስረዳው ይጠይቃል። አባትም እንዴት አድርጎ ቢያስረዳው በቀላሉ ሊገባው እንደሚችል ትንሽ አሰብ አድርጎ እንዲህ ይገልጽለታል።አየህ ልጄ ካፒታሊዝም ማለት አንዱ በገንዘቡ ብዙዎችን የሚቆጣጠርበት ሥርአትነው። ባለገንዘቡ ካፒታሊስት ይባላል።

በካፒታሊዝም ሥርአት መንግስት ህዝብን የሚያስተዳድርበት ሠልጣንና ገንዘብ የሚያገኘው ከካፒታሊስቱ ስለሆነ ካፒታሊስቱ ሠራተኛውን ክፍል እንደፈለገ ቢያደርግ ምንም አይልም።ህዝብም በደሉን እያየ ምንም ማድረግ ስለማይችል ዝም ይላል።

ለምሳሌ የኛን ቤተሰብ እንደ ካፒታሊዝም ሥርአት ብንወስደው እኔገንዘብ ስለማመጣ ካፒታሊስት ነኝ። እናትህ ደግሞ ገንዘቡን ተኔ ተቀብላ ቤተሰቡን ስለምታስተዳድር መንግስት ማለት ነች።አንተና ወንድሞችህ ደግሞ ህዝብ ስትሆኑ= ሞግዚታችሁም ሠራተኛው ክፍል መሆኗ ነው።ብሎ በምሳሌ ያስረዳዋል።

ልጅም የአባተን አገላለጽ በማንሰላሰል ውሎ ይመሸና ይተኛል።አልጋውም ላይሆኖ ሲያስብ ቆይቶ እንቅልፍ ሸለብ እንዳደረገው ድንገት የሚንጓጓ ድምጽ ይሰማናብንን ብሎ እናትና አባቱ ወድተኙበት አልጋ አቅጣጫ ሲመለከት እናቱ ብቻኘ ተኝታ ያያል።አባቱን በአይኑ ሲያፈላልግ የሚንጓጓው ድምጽ አሁንም ከወደ ሞግዚቷ ክፍል ተሰማው ።

ኘቀስ ብሎ ሄዶ በጭላንጭል ሲመለከት አባቱ በሞግዚቷ ላይ ሰፍሮ ያየዋል። ልጅም የአባቱን ነውርኘ መመልከቱ እንዳይታወቅበት ቀስ ብሎ ኮቴ ሳያሰማወደ መኝታው ይመለሳል።በማግስቱም አባቱና እናቱ በተቀመጡበት ይሄድና አባቱን እንዲህ ይለዋል አባዬ ትናት ስለ ካፒታሊዝም ያስረዳኸኝ አሁን ገና በደምብ ገባኝ ሲለው አባትም ደስብሎት ጎሽ ልጄ እስኪ እንዴት እንደገባህ ንገረኝ ይለዋል።

ልጅም ሲያስረዳ፥ አንተ እንዳልከው ካፒታሊዝም ሰራተኛውን ክፍል እየተጫነው ሲያጠቃው መንግስት ዝምሎ ተኛ። ህዝብ ደግሞ ምንም ማድረግ ስለልቻለ በደሉን አይቶ ዝም አለ ብሎ ሳይጨርስ በቃ በቃ ልጄ በደምብ ገብቶሃል በቃ ጎሽ ጎሽ ብሎ ጉዱን ሚስቱ ሳትሰማ የልጁን አፉ አዘግቷል።